ከዕለታት አንድ ቀን ሁለተ ወንድማማተ ዝንጀሮዎት በአንዲት ዝንጀሮ ወዳጃቸው ይጣላሉ፡፡
አንደኛው ለሁለተኛው፤
"እንግዲህ እዚች ሚስቴ ዝንጀሮዬ ጋ ድርሽ እንዳትል" ይለዋል፡፡
ሁለተኛው፤
"አይ ወዳጄ እኔ ልልህ ያሰብኩትን ነው አንተ አሁን ያልከው፡፡ የሀሳብ መመሳሰል ያስገርማል፡፡ ዞሮ ዞ
እዚች ሚስቴ ጋ ድርሽ ካልክ በራስህ ፈረድህ"
አንደኛው
"እንዴት?"
ሁለተኛው፤
"ሚስትነትዋ ያለጥርጥር የእኔ ነው፡፡ አርፈህ ተቀመጥ"
አንደኛው፤
"አርፈህ መቀመጥ ከቻልክ አንተው አርፈህ ተቀመጥ! አለዛ እንግዲህ እንዴት በቡጢ
እንደማንገጫግጭህ ስታይ ዋጋህን ታውቃለህ!"
ሁለተኛው፤
"አንተ እኔን?"
አንደኛው፤
"አዎ አንተን ምናባክ እንዳትሆን ነው?"
ተጋጋሉ፡፡ ሁለቱም ለቡጢ ተቀራረቡ! ተሰነዛዘሩ፡፡ ሌሎች ች መጡና ከበቡዋቸው፡፡ ጩኸት በረከተ!
የሠፈሩ አለቃ የሆነው የሁለቱ ወንድማማች ዝንጀሮዎች አባት መጣና ገላገላቸው፡፡
ሁሉም ፀጥ እርጭ አሉ፡፡
አባት፤
"እሺ የፀቡ መንሥዔ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀ፡፡
አንደኛው፤
"ሚስቴን እየነካ አስቸገረኝ"
ሁለተኛው፤
"እኔንም ሚስቴን እየነካ አስቸገረኝ"
አባት፤
"ሁለታችሁም ስለአንዲት ዝንጀሮ ሴት ነው የምታወሩት?"
አዎን አሉ ሁለቱም፡፡
"እንግዲያው" አለ አባት "ይቺ ዝንጀሮ ትጠራና ትምጣ" አለ፡፡
ዝንጀሮይቱ ተጠርታ መጣች፡፡
አባት፤
"ይሄኛውም ልጄ የአንቺ ባል ነኝ ይላል፡፡
ይሄኛውም ልጄ የአንቺ ባል ነኝ ይላል...የትኛው ነው ትክክለኛ ባልሽ?"
ዝንጀሮይቱ ራሷን ደልደል አድርጋ ተቀመጠችና፤
"ጌታዬ፤ ከእነዚህ ልጆችዎ አንዱ እንኳ ዕውነተኛ ባሌ ቢሆን ከእኔው ጋር እቤቴ ተቀምጦ ያገኙት
አልነበር? አርፎ የተቀመጠ ልጅ ኖሮዎት ያቃል?" ስትል መልሷን በጥያቄ አጠቃለለች፡፡
አባት፤
"እግዜር ይስጥሽ ያቺንም ያቺንም እየነካኩ ባል ነኝ ማለት አቋም የለሽነት ነው፡፡ አሳዳጊ የበደለው ልጅ